

# «ዝንቦም»
# እንደ
# «ንቦ!»

## (ያገጣጣሚ ተምሳሌት)



(ገሞራው - ዘስዊድን)

ይህች ዝንተ ዓለሚን፣ በፍዳና በደይን ነበልባል ዕሳት እየጋየችና እየተቃጠለች የምትኖር አገር፣ አሁን ደግሞ ቆዳውን እንደ ዕባብ ገልፍፎ፣ በአዲስ ክሥተት የገዘፈው ነባር ጠላቷ፣ ሰሞኑን ቀርቧል። እጅግ የሚደንቀው፣ በሌለበት የተፈጥሮ ጠባዩ፣ «ንብ» ነኝ ብሎ፣ ራሱን አስመስሎ መቅረቡነው። በዚህም ሐዳስ ድርጊታዊ ተውኔቱ የተነሳ፣ የአንድ መጽሐፌ ትንግርተኛ ይዘት ትዝ አለኝ። ግዙፍ ልብወለድ (novel) ነው። ባለሺህ ገጽ! ከተዘጋጀ ብዙኃን ዓመታት አስቆጥሯል። በዲናሮች እጥረት አልታተመም። «ዲሞክራሲያ» (የዝንቦች - ስለማር - እንደ ንብ አስተዳደር!) ይባላል! እንዳጋጣሚ ድሮ አንድ ወቅት ላይ፣ ታሥሬ በነበረበት ወቅት፣ መጽሐፉም ከኔው ጋር ታሥሮ ስለነበር፣ የጊዜው የካቢኔ ሚኒስተር የነበረው አቶ ነቢያ ልዑል ክፍሌ፣ ለንጉሡ አቅርቦ ማስነበቡ ትዝ ይለኛል። በንዴት....

እንደ አጋጣሚ ዛሬ፣ የሀገራችን ቁንጮ ነኝ ባይ ደምባራ፣ በዘንድሮው የምርጫ ወቅት፣ ዓይን ባወጣ የአደባባይ ድፍረቱ «ንብ» ነኝ ብሎ፣ ለውድድር መቅረቡን ሰማሁ። የመጽሐፉን የዝምብ ታሪካዊ ይዘቱን ትዝታ፣ ይህ ልዩ አጋጣሚ፣ ሰሞኑን ቀሰቀሰብኝና ነው፣ ዛሬ ይህችን ግጥም ያቀረብኩት። አግኝታችኋት የምታነቡልኝ ወገኖች ሁሉ እመኑኝ።

በዚህ ዓለም ያሉ - አንዳንድ ትንግርቶች፣
ዕፁብ ድንቅ ናቸው - ሲያያቸው ተመልካች።

ከነዚህም አንዱ - የዝንቦች ታሪክ ነው፣
በአንድ ዘመን ላይ - በገሐድ የታየው።

ኑሮ የሰለቻቸው - የአንድ ወቅት ዝንቦች፣
ሊቀይሩ አሰበው - የሕይወትን ልምዶች።

እንዴ ተጠራርተው - ተሰበሰቡና፣
ማር እናምርት አሉ - ያለው ልዩ ቃና።

ባሰቡበት መንገድ - ተባብረው ሊሰሩ፣
ዕቅድ አዘጋጁ - ተግባራት ተጋሩ።

ለሁሉም ዘረአ ዝንብ - ሥራ ተመደበ፣
በዚያም ተሠማራ - ሙያውን ገደበ።

አንዱ ውሃ ሊያግዝ - ሌላው ፖለን ሊለቅም፣
ለያንዳንዱ ሥራው - ተሰጠው እንደአቅም።

ተግባር ማስፈፀያም - ደንብና ሕግ ወጣ፣
ሲለግም የሚገኝ - ሆኖ የሚቀጣ።

Posted on www.debteraw.com on 22 February 2007 by courtesy of the poet.

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

እንዲያ ተጀምሮ - ማምረቱ ሲካሄድ፣
ማክበር አልተቻለም - የሕግጋቱን አምድ።

ወሃ ለማጓጓዝ - ከምድብ ሠራዊት ፣
መንገድ ሲያጋጥመው - ደማም ዝምቢት ድንገት፣
በዚያው ይቀልጥ ጀመር - ስሜት አስገድዶት።

ለዚያ አይነት ወንጀሉ - ድንጋጌው ቅጣት፣
አንቴና መቁረጥ ነው - ያለምንም ምሕረት።

መንገድ ከወደቀ - የአህያ በክት ላይ፣
ሲከልክስ ቢገኝ - የዝንብ አንድ ኮብላይ፣
ቅጣቱ ነበረ - አንድ ክንፉን ማጣት፣
ከስራው ላይ ባልጎ - ስሕተት ለሠራበት።

ልምዱ እያሸነፈው - ወንጀሎች ሲፈጽም፣
በዚያው ልክ ሲቀጣ - አካሉን ሲያዳክም፣

ዝንብ ዘር አለቀ - የትም ተረፍርፎ፣
ክንፍ አንቴና አጥቶ - አካሉም ረግፎ።

የስራቸው ውጤት - ምንም ቢዋትቱ፣
ከዳ ብቻ ሆነ - መጨረሻ ምርቱ።

ሌላ ልዩ ዘዴ - እንፈልግ ብለው፣
መተራመስ ያዙ - በየግል ሙያቸው።

በመጨረሻ ላይ - እኛ አልቻልንም ብለው፣
አማካሪ አመጡ - ጥቂት ቢረዳቸው።

ንብ ነበረች አንዷ - የመጣች ልትረዳ፣
እሷም በበኩሏ - ርዳታውን ወዳ።

ቀስ ብላ በጥበብ - እየተጠቀመች፣
ዝንብን ባሪያ አድርጋ - መመጥመጥ ጀመረች።

ውሃውን ፖለኑን - ቁጭ ብላ እያስጋዘች፣
በዝንቦች ጫንቃ ላይ - ተንቀባራ ኖረች።

ዝንቦች ተበሳጭተው - በሆኑት ሁኔታ፣
ተበታትነው ቀሩ - አላንዳች አለኝታ።

ዘመናት ተሻግረው - በአሁኑ ዛሬ፣
ደግሞ ዜና ሰማሁ - ልዩ ቅይር ወሬ።

ያልሆነውን ሆነ - ንቦች ነን የሚሉ፣
በዚያ ባገራችን - ተገኝተዋል አሉ።

Posted on www.debteraw.com on 22 February 2007 by courtesy of the poet.

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ንብስ አትመስለኝም - በሚታየው ግብሯ፣
ለማስመሰል እንጅ - አሳፈጣጠሯ!

ዝንቦ ትሆናለች - እንደዚያ የምትል፣
ሰዎችን መርዛ - አሳዳ የምትገድል!

ይህም ይታወቅ ዘንድ - መግደል ጀምራለች፣
ደካማውን መርጣ - አጭዳ ከምራለች፣
ለሆዷ እንዲሆናት - ደም አጠራቅማለች።

ለምን ገደልክ ብሎ - ክርክር አያምርም፣
የዝንብ ተፈጥሮ ነው - የግድ መኖር በደም።

ሕግ አምክንዮ - ሥርዓት አለ ሎጂክ፣
ሃቆችን ማስረጃ - የተገኘ ካምላክ፣
በዚያ መከራከር - ያዋጣል ሊያሳይ ልክ።

ለምንስ ይገድሳል - ማለት አያዋጣም!
ምንም ሎጂክ የለው - የትም አያደርስም!
መኖሪያው ከሆነ - ሕይወቱ በሰው ደም።

የመጣችሁ ዛሬ - ለማለት አትግደል፣
ልትሉ እንደሆነ - በማኅበር በግል!

ተሳስታችኋል - ልክ አይደላችሁም!
እንደዝምብነቱ - ግብሩ አልገባችሁም!
በሌላ እንዴት ይኑር - እንበለ ምግቡ ደም?

ድንጋይ መብላት አይችል - ወይም አፈር ቅጠል!
ተፈጥሮው አይደለም - ያን መመገብ መቻል።

ስለዚህ ይልካል - ነፃ አውጭ (አግዓዚ) ሠራዊት!
ፈልጎ የሚገድል - ለጋዎች ሕፃናት።

ንብ ነኝ ትበል እንጅ - ንብ ልትሆን አትችልም፣
እሷ በፍጥረቷ - ደም  አትበላ አትጠጣም፣
ካበባም በስተቀር - ሌላ አትመገብም።

ስለዚህ ሎጂኩ - በዚሁ ይግባችሁ፣
ንብ ሊሆን አይችልም - ንብም ነኝ ቢላችሁ።

ዝንቦም እንደ ንቦ - ነኝ እያለ ቢሰብክ፣
ከቶ አትቀበሉት - ስለሌለው ሎጂክ!

ማስረጃው አንድ ሃቅ - የሎጂክ ብሂሉ፣
ከቶ ለምን ይሆን - ሕፃናት መግደሉ?
ለደም ፍለጋ እንጅ - ለተፈጥሮ ዓመሉ።

Posted on www.debteraw.com on 22 February 2007 by courtesy of the poet.

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ንቢትማ ቢሆን - ደም ምን አስፈለገው?
በንብነት ባሕሉ - አይበላው አይጠጣው።

ንብ አለመሆኑን - ያገሬ ሕዝብ አውቆ፣
ወዲያ ሃች ጥሎታል - አሽቀንጥሮ አርቆ።

ደግሞኮ መድፈሩ - ምረጡኝ ማለቱ!
ራሱ እያወቀው - ለመሆኑ ከንቱ!

ለዚህ አይደለም ወይ - ዘረፉ የገባው፣
ኮሮጆ ቀዳዶ - ድምፆች የዘረፈው።

ያረገውን ቢያደርግ - ሕፃናት ቢያደማ፣
ከእንግዲህ አይደርሳት - ከሥልጣኑ ማማ!

ጎበዝ ተረዳድተህ - ይቺን ዝንብ አስወግድ፣
አግዛ አምጥታ - የመርዞች አዕማድ፣
ያ ወገንህ ከሚያልቅ - በጥይት ነጎድጓድ!

ደም ይወዳል ዝንቦ - ያውም የሕፃናት፣
ተዘጋጅቶ ሲቀርብ - ባግዓዚ ጥይት!

የቆላ ዝንብ ነበር - የሚፈራማ ጥንት፣
የበረሐው መጣ - ሰሞኑን በድንገት፣
ንቦ ነኝ እያለ - ቀይሮ ሰውነት፣
አርዶ ሊጠጣ ደም - የየዋህ ሕፃናት።

የቆሌው ባለሟል - ልክስክሶ ዝንቦ፣
ንብ ነኝ ብሎ ይምጣ - ሠራዊት ሰብስቦ፣
ሊያርድና ደም ሊያፈስ - ካንጀቱ አስቦ።

ለብዙ አዝማናት - ብትሞክር ብትሞክር፣
ያንን ማር ለመሥራት - ጠዋት ማታ ብትጥር፣
አልሆንላት ብሏት - ዝምብ አድርጓት እግዜር!

በመጨረሻ ላይ - እጅግ ተስፋ ቆርጣ፣
መረፍረፍ ይዛለች - ባመጣባት ጣጣ።

ያመጣቻቸውም - አማካሪዎቿ፣
ምንም ፋይዳ አልሰሩም - ሆኑ መዛበቻ።

የድካሟ ሁሉ - የሥራዋ ውጤት፣
ከዳ ብቻ ሆኖ - እጅግ አበሳጫት።

በዚያም የተነሳ - የምትሠራው ወንጀል፣
ተቆጥሮ አያልቅም - የሌለው ነው አምሳል።

Posted on www.debteraw.com on 22 February 2007 by courtesy of the poet.

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com

ዝንብነቷን አውቀው - ማጥፊያ መርዝ ሲረጩ፣
ቱባ ጎምቱ ሰዎች - ቢሄዱ ሲያንጫጩ፣
«እኔ ንብ ነኝ» አለች - ነገር አታጋጩ!

እንደውም በዘዴ - አድብታ በመምጣት፣
በደንብ ለመታየት - ደረት ላይ ፊት ለፊት፣
በካናቴራ ላይ - ገዘፈች ግድ የላት!

ትልቅ ክብርኮ - አቅምን አውቆ መኖር፣
እንደተፈጠሩ - ያለመደናበር!
ያልሆኑትን ሆኖ - አጉል ከመግደርደር።

ዝንቦም እንደ ንቦ - ልሁን ብሎ መጣር፣
በሲኦል እያሉ - በገነት ውስጥ መኖር፣
ይመስላል ንፃሬው - በምኞቱ አንፃር!

ቢቀርባት ይሻል - አጉል መንጠራራት፣
ምድረ ፋይድ እያለች - አርያም መመኘት።

ማር እንደሚሠራ - ንቦን ልሁን ማለት፣
ዝንቦን አያዋጣም - አጉል መንጠራራት!

እንደ ሆነች ሆና - ብትኖር ይሻላታል፣
ከዝንብነት ውጭ - የላትም ሌላ ዕድል!!!

አያመጣው የለ - የዘመን ቀባጣ!
ልክስክሱም ዝንቦ - ንብ ነኝ ብሎ ይምጣ?

የቆሸው ባላባት - ሰውን አታለለ!
ግንባር ፊደል ቆርጦ - ንቦ ነኝ እያለ!



እዚሁ ላይ ይብቃኝ - ምሥጢሩም ይኸው ነው፣
ዝንብ አይጫወትም - በኢትዮጵያዊው ሰው!

****** (ገሞራው - 1997 የሒሳብ መስጫ ቀን) ******

Posted on www.debteraw.com on 22 February 2007 by courtesy of the poet.

PDF created with pdfFactory trial version www.pdffactory.com